ኢትዩ ብሔራዊ ት/ቤት

የ2012 ዓ.ም የ4ኛ ሩብ ዓመት ለ12ኛ ክፍል የተዘጋጀ አጭር የዕለት ት/ት

☛ ውድ ተማሪዎች፡- <u>ይህን ማስታወሻ በደብተራችሁ ከገለበጣችሁ በኋላ መልመጃዎችን ስሩ፡፡</u>

የትምህርት ዓይነት፡- <u>አማርኛ</u> **<u>ለ12ኛ A- D ክፍል</u>**

ምዕራፍ፡-

ርዕስ ፡-

ንዑስ ርዕስ ፡-

ገፅ፡-

<u>ሰኞ ግንቦት 17/2012 ዓ/ም</u>

ሙዚቃው፣ሰዓሊው፣ጸሀፌ ተውኔቱ፣መራሄ ተውኔቱ (አዘጋጁ)፣ የመብራትና የድምፅ ባለሙያው...ባንድላይ ጥበቡን አዋጥቶ ድራማውን ከየአቅጣጫው ይከሽነዋል፡፡

- **ጸሀፌ ተውኔት፡**-የድራማውን መሠረታዊ መላክ የሚነድፈው ደራሲ ጸሀፌ ተውኔት ይባላል፡፡
- **ቃለ ተውኔት፡-** በድራማ ውስጥ ከሁለት ወይም ከዚያ በላይ በሆኑ ገፀ-ባህሪያት (ተዋንያን) መካከል የሚደረግ ንግግር ነው፡፡
- **ተዋንያን፡-** በፀሃፌ ተውኔቱ ድራማው ከተፃፈ በኃላ በውስጡ ያሉትን ገፀ-ባህሪያት ስብዕና፣ ውስጣዊ አስተሳሰብ እና ማንነት፤የራሳቸው አድርገው በመድረክ ላይየሚተውኑ የጥበብ ሰዎች ናቸው፡፡
- **የተውኔት መዋቅር**፡-የተውኔት አላባውን (መቼት፣ ሴራ፣ ቃለ-ተውኔት እና ጭብጥ) በተገቢው መንገድ ተዋህደው ሲቀርቡ የሚገኘው ቅርጽ የጠውኔት መዋቅር ነው፡፡
- **የውጠት ደረጃ፡-** ገፀ-ባህሪያቱ፣ አጠቃላይ እና ውስን መቼየቱ፣ ግጭት፣ ርዕሰ ጉዳይ እና ድባቡ የሚተዋወቁበት ነው፡፡
- **ጡዘት፡-** ከገፀ-ባህሪያቱ የሚመነጨው መስተጋብር ቀስ በቀስ ያድግና ይጦዛል፡፡ በዚህ ሂደት ግጭቱ ወደ መፍትሄ ይሸጋገራል (ቅልበሳ ይካሄዳል)፡፡ በመጨረሻም ፍፃሜው (ልቀቱ) ይከሰታል፡፡ በዚህ አይነት ድራማው የዝቅጠት ደረጃን ያጠናቅቃል (ይፈፀማል)፡፡
- **ገቢር፡**-ገቢር የድራማው አብይ ክፍል ነው፡፡ ድራማ በገቢር ተከፋፍሎ ሲቀርብ ከአንዱ ወደ ሌላው ገቢር የሚደረገው ሽግግር ብዙውን ጊዜ መጋረጃ በመጣል(መብራት በማጥፋት) ይከናወናል፡፡

- **ትዕይንት፡-**የገቢር ንዑስ ክፍል ሆኖ አከፋፍሎ እንደገቢር የድራማውን ድርጊት የሚፈፀምበት ጊዜ ወይም ቦታ መለወጡን አያመለክትም። በትዕይንት አከፋፈል ላይ ወጥ የሆነ ፀሃፌ ተውኔት እና ሃያሲያን የሚከተሉት አሰራር የለም።
- **መነበባንብ**፡-የገፀ-ባህሪያትን ስውር ህሊናዊ መልክ ለተደራሲያን ለማሳየት ሲባል ገፀ-ባህሪው በዙሪያው ሌሎች ገፀ-ባህሪያት በሌሉበት ጊዜ ለራስ እና ለተደራሲ የሚያነበንበው የግል ንግግር ነው።
- **ጎንታ፡-** ተናጋሪው በመድረክ ላይ አብረውት የነበሩት ገፀ-ባህሪያት እንደማይሰሙ በመቁጠር ለራስና ለተደራሲያን በሹክሹክታ ፊቱን ወደተደራሲያን አዙሮ ከፍባለ ድምፅ የሚናገረው የብቻ ንግግር ነው። (ድብቅ የሆነው ፍላጎት የሚገለፅበት ነው)።
  - የተውኔት አላባውያን የሚባሉት ፡-ቋንቋ፣ ሴራ፣ ገፀ-ባህሪያት፣ ትዕይንትና ሙዚቃ ናቸው።

ማክሰኞ ግንቦት 18/2012 ዓ/ም

ተውኔታዊ መዋቅር (ካለፈው የቀጠለ) ማስታወሻ

እውቂያ፡ በዘልማዳዊ ተውኔታዊ መዋቅር ውስጥ ከሚካተቱት አብይ ክፍሎች ማለትም ከመጀመሪያው፣ መካከለኛና መጨረሻ በቀዳሚነት የምናገኘው ነው። የተውኔት ታሪክ ተዳምሮ በደንብ ከመጉላት በፊት ለተደራሲያን አጠቃላይ መረጃ የመሰጥበት ክፍል እቅቂያ ይባላል።

ትውስብ፡- ከውቂያ አሰረጫጨት በመቀጠል የሚመጣ የተውኔታዊ ሴራው ወሳኝ ክፍል ነው። ከዚህ ክፍል አስቀድሞ የተመሰረተውና በሚገባ የዋቀረው ግጭት ልብን በመስቀል እስከ ጡዘት ድረስ ይወሰሰባል።

ውጠት፡- ከመጀመሪያው እስከ መካከለኛው ያለው የተውኔዊ ሴራው(ትልሙ) ክፍል ነው። ሴራ(አፅመ ታሪክም) ይባላል።

ጡዘት፡- የተውኔት ግጭት የሚፈልገውን ያህል አየተወሳሰበና እየከረረ ሲጓዝ ይቆይና እድገቱን የሚደርስበት ቦታ ነው።

ዝቅጠት፡- በዘልማዳዊ ተውኔታዊ መዋቅር ከጡዘት ቀጥሎ የሚከሰት የሴራው የመጨረሻ ክፍል ነው። በዚህ ክፍል እስከ ጡዘት ድረስ ሲጎነጉንና ሲሸርብ የነበረው ግጭት ተመልሶ የሚተረተርበት ወይም እልባት የሚሰጥበት ይሆናል። በዝቅጠት ተውኔታዊ ድርጊቶች የአስልችነት ስሜት በታዳሚው ዘንድ እንዳይፈጥሩ በፍጥነት ወደ መደምደሚያው መጓዝ ይጠበቅባቸዋል።

ቅልበሳ፡- የግጭት መርገብና የሀሳብ መታረቅ የሚፈጠርበት ክፍል ነው።

ልቀት፡- በዘልማዳዊ ተውኔታዊ መዋቅር (በልበለዳዊ መዋቅር) ውስጥ ከሚገኙት አብየት ክፍሎች የመጨረሻውና ወሳኝ ክፍል ነው። ንዑስ ግጭቶችን አመክኗዊነቱን በጠበቀ መልኩ አንድ ባንድ እልባት የሚጥባቸው ክፍል ነው።